# (ክፍል 2) የግንቦት 7 ምሁራን ተከታዮችና ጋዜጠኞቻቸው ከኤርትራዊያን የቀሰሙት "ውሸትን የማግዘፍ!" አዲስ ትምህርት!

ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ) Ethiopian Semay getachre@aol.com

ወደ ጽሑፌ ከመግባቴ በፊት አንድ መልእክት ላስተላልፍ። **"የመለስ ራእይ ሲፈተሽ"** የሚል **የአስገደ ገብረስላሴ** አዲስ መጽሐፍ መነበብ ያለበት መጽሐፍ ስለሆነ አፈላልጋችሁ ማንበብ ይኖርባችኋል። በጣም ፤በጣም በጣም፤በጣም እጅግ በጣም የመለስ ዜናዊ ወስጣዊ ባሕሪ፤ የሥልጣን ጥማት፤ እና ጨካኝነት በጥልቀት የዳሰሰ ጥናት አና "አድርባይ ምሁራን አድናቂዎቹ በመጽሐፍ መልክ እና በመጽሔት መልክ የጻፉትን ሃሰተኛ የመለስ ርህሩሕ ለሰው ሕይወት አዛኝነት፤ ዲሞክራቲክ ባሕሪ፤ አገር ወዳድነት እንዲሁም ፈላስፋነት" ምን ያህል በሃሰት የተቀባ ውዳሴ መኖሩን በጥልቀትና በቀላል አቀራረብ ከነማስረጃው በበቂ አስደግፎ የተነተነ አሁን ላለውና ለመጪው ትውልድ የሚጠቅም መጽሐፍ ስለሆነ አንድታነብቡት ምክሬን እለግሳለሁ።

በጽሑፉ ላይ አንዳንድ ጥቃቅን ነገሮች ላትስማሙ ትችላላችሁ እኔም አለኝ፤ ግን በሳላ/ጠንካራ ፍሬው ያመዝናል። ጊዜ ሲፈቅድ በግምገማ እመለስበታለሁ። ይህ የኔ አጭር ማስተዋወቅ ብዙ ሰው እንደሚገዛው አውቃለሁ። አስገደ ገብረስላሴ ቆራጥ የወንዶች ወንድ መሆንክን ማሳያ አርአያነትህን በማሳየትህ አጅግ አመሰግንሃለሁ። ሌሎቻችሁ (ገብሩ አስራትን ሳይጨምር) የተቀራችሁ "የቁም ሙታኖች" ግን ወደ እናታቸው ማህጸን ተመልሳችሁ ብትገቡ ምንኛ ጥሩ ነበር። አሁን ወደ ርዕሴ ልግባ፤-----

ባለፈው ሰሞን ስለ የግንቦት 7 ሁለት መሪዎች ወደ ኤርትራ ማቅናታቸው ተከትሎ ተከታዮቻቸውና አድናቂዎቻቸው እንዲሁም ጋዜጠኞቻቸው የቀባጠሩት ታቦትን የማምለክ የሚመስል እና የዓድዋ ጦርነት እያመሳሰሉ የጻፉትን እና ጋዜጠኛ ደምስ የተባለ ሞስኮ/ሶቭየት ሕብርት በጋዜጠኛነት ሙያ የተማረ ጠንካራ ጋዜጠኛ የዘለፉበትን (ታሪኩ አባዳማ የተባሉ ጸሐፊ ኢትዮሚዲያ ተለጥፎ አሁንም ያለውን ስድብና የንቀት ጽሑፍን ልብ ይለዋል)፤ በየፓልቶኩ የተቀደዱት አምላኪዎቻቸው በሚመለከት ጆሮአችን በመደንቆሩ የግድ የዋሃን የበዙበት ወቅት ስላላን ስለ ግንቦት 7 ምንነት እና መሪዎቹ ስለ አማራ ማሕበረስብ ያላቸው ጥላቻ፤ ስለ አንድነታችን (በዲሞክራሲ/ሪፈረንደም ተጠቅሞ አገር ማፍረስ የፈለገ ካለ መብቱ እንደሚጠብቁለት የሚለው አቋዋማቸውን) እና ስለ ሉዓላዊ ግዛታችን፤ወደባችን፤ እና ድምበሮቻችን ሁሉ ልክ ከመለስ/ወያኔ እና መሰል ተከታዮቹ የሚለያቸው ነገር እንደሌላ በመረጃ ደጋግሜ ገልጫለሁ።

ወያኔዎች ለኤርትራዊያን ተብየዎች አሳልፈው የሰጡዋቸው ሉዓላዊ ክብሮቻችንን እና ስለ እነሱም ጥብቅና ቆመው እንደተሟገቱላቸው ሁሉ፤ የግንቦት 7 አመራሮችም እንዲሁ ስለ ኤርትራም ሆነ ስለ ኢሳያስ አይታ፤ ለወደፊቱ የሚከተሉት መመሪያ እና ንግግራቸው ካሁን ከጅምሩ ብልጭታው እንደ መብረቅ የማስጠንቀቂያ ምልክት እያየን ነው።

ወያኔን ያለ ጠመንጃ በሰላማዊ ልገማ ወደ ድርድር ማምጣት እንደሚቻል ፍንጭ ያሳየንን የቅንጅት ትግል አፍርሶ ወደ አሜሪካ የፈረጠጠው ብርሃኑ ነጋ እና ጉጅሌው፤ እዚህ እንደመጣም ከአጃቢ ምሁራኖቹ እና የመድረክ አስተዋዋቂዎቹ ሆኖ በለመዚን እና በጉንጉን አበባ መስተንግዶ እየተደረገለት በየከተማው እየዞረ (ብርቱካን መዲቅሳንም አብራው ቅንጅትን የማደፍረስ ሚናዋን አትርሱ) አንድነታችንን ለሁለት ከፋፍሎ ከፍተኛ የሆነ አፍራሽ ስራ እየሰራ ቆይቶ ከብዙ አመታት ማመንታት/'ፈራ ተባ' ወደ ኤርትራ ጠቅልሎ መጓዙንና (አንዳንዶቹ አሜሪካውያን ናቸው የላኩት የሚል ጥርጣሬ አለን ይላሉ! እኔ አላልኩም)፤

ቢሄድም በወያኔ ምትክ ሻዕቢያን ለማገልገል እንጂ የረባ ብሔራዊ ጠቀሜታ ያለው ለውጥ ለማስገኘት እንዳልሆነ በዛው ጽሑፌ ላይ የዋህ ክፍሎች በሚያደነቁሩን እልልታ የሚመጣ ነገር እንደሌለ  ምክሬን በጨረፍታ እንደጠቀስኩ ይታወሳል።

በእንጥልጥል የተውኩትን ክፍል 2 እነሆ፤-

..... አበባ ዮሴፍ የተባለቺዋ ኤርትራዊት፤ ኤርትራ ውስጥ አስመራ ከተማ ካለው የሻዕቢያ ራዲዮና ቴ/ቢዥን ጣቢያ ወደ ኢትዮጵያ የሚተላለፈው ፕሮግራም ውስጥ እዛው በመሸጉት ኢትዮጵያ ተቃዋሚ ተዋጊ ሃይሎች አነግን ጨምሮ፤ ያልተደረገ ጦርነት እንደተደረገ በማስመሰል ጦርነት የተደረገበት የቦታ ስም እና የተማረኩ ወይንም የሞቱ የወያኔ ወታደሮች በሻዕቢያ የዜና ሃላፊዎች የፈጠራ ዜና እየተጻፈ ለምሳሌ ለኦነግ ለእነ ዳውድ ኢብሳ አስጠርተው ዜናው እንዲመለከቱትና እነሱም ያላቸው የፈጠራ ዜና ካላቸውም ጨማምረው እንዲያጣፍጡት በማድረግ ሃሰተኛ ዜና ይተላለፍ እንደነበረ ገልጻልናለች (መረጃው ለማግኘት "አበባ ዮሴፍ ኤሪትርያን ጆርናሊሰት/"
Eritrean journalist Abeba Yousef Part II
https://youtu.be/n3h13EGd9wI

ብላችሁ ዮ-ቱብ ብትገቡታገኙታላችሁ)።

በዛው የፈጠራ ስራ የሚያቀናብሩ እነ ማን እንደሆኑም በስማቸው ፤ ለምሳሌ መኩርያ ወልዱ የተባለ የሚዲያው ሃላፊ የመሳሰሉትን እየገለጸች፤ መቸ እንደተላላፈ ሻዕቢያን ከድታ ከባልዋ ጋር ለኢትዮጵያ እጇን ከሰጠች በኋላ በዝርዝር የገለጸቺው ተከታታይ ያለው ቃለ መጠይቅ

ስታደምጡ የሰሞኑን "ፊሽካው ተነፍቷል" (የዓድዋው ጦርነት!!!) የኢሳቱ መሳይ መኮንን የቃለ አጋኖ ፎሽፈሽ (ወሬ) በቀላሉ ሊገባችሁ ይችላል።

የግንቦት 7 ራዲዮ/ቴቪ አፈልጋይ የሆነ ኢሳት የተባለው "አድላዊ" እና ቱልቱላ ጣቢያ ግንቦት 7 ከወያኔ ወታደሮች ጋር የከፈተበትን ስዕለ ድምፅ (አውዲዮ ቪዲዮ) ብሎ ያቀረበው በጣም እጅግ የቆየ አርበኞች ግምባር ያከናወኑት የጦርነት ፋይል/ክንዋኔ ነው የተባለለትን ስዕል እንደ አዲስ አድርጎ በማቅረብ "የዓድዋ ጦርነት" ተጀመረ ብለው የሰበኩበትን አውነታው እንዲህ ያለ የፈጠራ/ወይንም ትንሿን ቶክስ "አጋንኖ የማቅርብ" የዜና ጥንቅር የተለመደ እንደሆነ ከአበባ ዮሴፍ ማድመጥ ትችላላችሁ።

ዘመዶቻችን ቁርጥምጥም አድርጎ ከበላብን እና አሁንም እያኘከብን ወደ ያለው የወያኔ የጅቦች ፋሺስታዊ መንጋ ትኩረታችን እንዳናደርግ፤ እጉያችን ውስጥ ሆኖ ሉአላዊነታችንን እና ወደባችንን በማናናቅ ሕዝባችንም "ነፍጠኞች" እያለ በመዝለፍ የተካኑት የኢሳያስ አፈወርቂ አሞጋሾችና የኤርትራ ኢሉአላዊ ጠበቆች የሆኑት የግንቦት 7 ድርጅት መሪዎች የሚከተሉት አደገኛ መመሪያቸው ለመቃወምና ለማጋለጥ ሳንወድ ገፋፍተውናል። ስለሆነም ስሕተታቸውና መመሪያቸው አርመው ይቅርታ እስካልጠየቁ ድረስ የሉዓላዊነታችን እና የሕዝባችን ክብር ለማስጠበቅ ተቃውሞኣችንን እንቀጥላለን።

ግንቦት 7 ከጥቂት ወራት በፊት ፤ ኤርትራ ውስጥ የተከናወነው በውህደት ስም የአርበኞች ግምባርን ድርጅት/ተዋጊና መጠሪያ መዋጣቸው/ መስነጋቸው (ሄጂሞኒ ማድረጋቸው) እዛው ለመሸጉ ኢትዮጵያዊ ሃይሎች (አርበኞች ግምባር ነባር ተዋጊዎች ማለቴ ነኝ) አደገኛ መሆኑን አጠር ያለ አንድ የውስጥ ጽሑፍ በኢንተርኔት በትኜ ነበር። ያንን አብራራልኝ ብሎ አንድ አንባቢዬ ስለጻፈልኝ ይህን ዕድል በመጠቀምና ሌላው የአዲስ ድምፅ ራዲዮ አዘጋጅ አበበ በለው ጉዳይም አብሬ ባጭሩ እተቻለሁ።

የበተንኩት ጽሑፍ የአርበኞች ግምባር ድርጅት በግንቦት7 መዋጡ- ስንታዘብ፤ ግሓት በተሓህት የመዋጡን ታሪክ ያስታውሰናል የሚል ነበር።_አዎን ውህደቱ "ንጥቂያ/ሄጂመኒ" ይባላል። ሁኔታው ልክ "ተሓህት" ምስራቅ ትግራይ አካባቢ መሽጎ የነበረው "ግሓት" ን በጠመንጃ በጉልበትና በዘዴ አታልሎ እንደሰነገው ሁሉ፡ ግንቦት 7ም ያለ ጠመንጃ በኢሳያስ መልካም ፈቃጅነት በአሳዛኝ ሁኔታ አርበኞች ግምባርን ውጦታል። "የወያኔና የብእዴን/ኢሕአዴንንም ታሪክ አስታውሱ። ይህ ድርጊት የግንቦት 7 ጠማማነትና የወያኔ መሰሪ አደገኛነት ሌላ ድርጅትን ወደ እራስ ለማጠቃለል የመዋጥ ባሕሪ የተከተለ ነው። አርበኞች ግምባር የተባለው ድርጅት **እርባና ያልነበረው** ቢሆንም ፖሊቲካዊ አመፅ ተፈጽሞበታል። "ሬፕድ" ሆኗል።ተዘርፏል! በትግርኛ መዘረፍ /መስረቅ ሳይሆን፤ ክብረ ድንግልናን መነጠቅ (መታመፅ) ማለት ነው።

ይህ ዝርፍያ አደገኛነቱ የተለያየ ጥፋትን ያስከትላል። በመጠኑም ቢሆን ወያኔ ድንገት ከውስጡ በሕዝቡ ወይንም ከእራሱ አባሎች “ጊዜ ከዶት” መከራው በላዩ ላይ እንደካብ ቢፈርስበት /ወይንም እኔ ከሞትኩ አገሪቷም ትሙት ብሎ ሥልጣን ልልቀቅ ቢል፡ አጋጣሚውን ተጠቅመው ሻዕቢያ፤ ኦነጎችና ኦብነጎች እንዲሁም የመሳሰሉ ፀረ አንድነት ሃይሎችና አክራሪ እስላሞች አሰፍስፈው እንደ የዱር አራዊት አገሪቷን ለመቀራመት ቢንጋጉ፤-

(1) **“አንገታቸው አቀርቅረው**፤ ማንነታቸውን ሳያስታወቁ አገር ውስጥ ያሉ “ወታደራዊ ልምድ ያላቸው” **ግምታቸው ለማወቅ የሚያስቸግር “አንዳንድ”** የህዋሕት ደሞዝተኛ አገር ወዳድ ወታደሮች/ መከላከያ ከሚሏቸው ውስጥ”

(2) ኤርትራ ውስጥ የሚገኙ የረባ ስራ ያልሰሩ እነዚህ “ለክፉ ቀን መከታ” ሊሆኑ **(ካንዳንድ የተሸጡ አርበኞች ግምባር መሪዎችን ሳትጨምሩ)** ይችሉ ይሆናል የሚል ግምት ያሳደርኩባቸው ኤርትራ ውስጥ **ጊዜ እስከያልፍ አንገታቸው አቀርቅረው ጊዜ እየጠበቁ ያሉ** “የኢትዮጵያ ሉአላዊነት” የሚያንገበግባቸው ፀረ ሻዕቢያ ተራ “የአርበኞች ግምባር” መሪዎችና ታጋዮች “ለክፉ ቀን” ይጠቅሙ ይሆናል የሚል ግምት **በመጠኑም** ቢሆን አለኝ። ሆኖም ግንቦት 7 በተራ ቁጥር 2 ያለው ድርጅት በኢሳያስ ፈቃድ ማንነቱን ስለተነጠቀ፤ ብርሃኑ ነጋ እና ኤፍሬም ማዴቦ እንዲሁም ንአምን እና አበበ (ኦነግ) ወዘተ የመሳሰሉ የድርጅቱ አመራሮች፤ ለኤርትራ ሉኣላዊነት ቀድመው የሚከላከሉ የህወሓት ፖሊሲ እና ባሕሪ የተከተሉ መሆናቸው በመረጃ ገልጫለሁ።

ስለሆነም **“ዓሰብ የነፍጠኞች መፈክር ነው!”** የሚለውን የግንቦት 7 መፈከርና ንግግር እንዲሁም **“ዓሰብ የነፍጠኖች መፈክር ነው!”** የሚለው “ድምሕት/ቲፒዲኤም” በፌስ ቡኩ፤ ያሰራጨው የትግርኛ መግለጫው/አዋጅና፤ እንዲሁም **“ዓሰብ የኢትዮጵያ ወደብ ነው የሚሉ ጦርነት የናፈቁ የነፍጠኞች መፈክር ነው!”** የሚለው የወያኔ እምነት፤ የግንቦት 7 መሪዎችና ድርጅታዊ እምነት (ኤፍሬም ማዴቦ ይህ ስናገር የድርጅቴ እምነት ወክየ ነኝ እየተናገርኩ ያለሁት ብሎ ኦክላንድ ካሊፎርኒያ ሻዓብያ ፌስቲቫል ተጋብዞ ግልጽ አድርጎልናል) ከወያኔ ጋር አብረው ስለሚጋሩ፤ግምቦት 7 መሪዎችም አርበኞች ግምባር ውስጥ ያሉት ነባር ታጋዮችም በዚህ እምነት “እንዲቃኙ” ያደረጋሉ።

*(ልክ ብዙ ትግሬዎች/ታጋዮችና ተከታዮቻቸው አሁንም ያንኑ መፈክር እንደተቀበሉት። ለምሳሌ ብጠቅስ የኢይጋም ሆነ የትግራይ ኦን ላይን አዘጋጆች ዐሰብን በሚመለከት በየድረገፆቻቸው የሚለጥፉትን ልብ ይለዋል። እንዲሁም “ሆርን” የተባለው ካናዳ የሚኖር የወያኔ ተከታይ በየፓልቶኩ ይህንኑ ለኤርትራኖች የሚወግን ተመሳሳይ የክሕደት ክርክር ነበር ሲያስተጋባ የቆየው፤ “ዓሰብ* ***የደርጎች*** *መፈክር” ነው ይላል። የፓልቶክ ስሙ “ሆርን” በመባል የሚታወቀው የትግራይ ሰው “ደርግ” እንጂ እንደ ግንቦት7 “ነፍጠኛ” አይልም )*

'የኢትዮጵያ' አርበኞች ግምባር (**'ኢትዮጵያ'** የሚለው ስማቸው በግንቦት 7 በውህደት ስም ከተዋጠ በኋላ እንዲሰረዝ ተደርጓል) በኤርትራ ያላቸው እኛ ያልተቀበልነው ሕጋዊ ያልሆነ የሉአላዊነት አቋም፤ በግንቦት 7 ፖለቲካዊ ትምህርት አሰጣጥ ለምሳሌ "የኤርትራ ሉዓላዊነትና የኢትዮጵያ ወደብ አልባነት" በሚመለከት እንደሕጋዊ እየተወሰደ በታጋዩ ሕሊና ውስጥ እንዲሰርጽ በመድረግ ታጋዮቹ ለኤርትራ ወግነው ጸረ ኢትዮጵያ ሊሆኑ ስለሚችሉ፤ "አርበኞች ግምባር" በብርሃኑ ድርጅት መዋጡ አደጋነቱ አያጠራጥርም ። ሻዕቢያዎች በሰራዊታቸው ውስጥ አስሰርጎ ሰላዮች ስለሚያስገባ (ኤርትራ አሰልጣኞች የነበሩ የተናገሩት ምስክርነት መረጃዎች በእጀተ ውስጥ አሉኝ) እነ ብርሃኑም ሆነ ማንም ድርጅት ለሰራዊታቸው የሚያስተምሩት ፖለቲካ በቅርብ ይከታተሉዋቸዋል።

በተለይ እነ ብርሃኑም ሆነ እነ አንዳርጋቸው በጦርነት ሳይሆን ጊዜአቸው ያሳለፉት/የሚያሳልፉት በፖለቲካ ቅስቀሳ ማስተማር ላይ ስለሚውሉ፤ መለስ ዜናዊ 'እልፍ ኣእላፍ' የተጣመመ የወያኔ ካድሬ አፍርቶ ጸረ ኢትዮጵያ ሉአላዊነት እንዲንቀሳቀስ እንዳደረገው ሁሉ፤ እዛ ያለው ገበሬና ውሱን ትምህርት ያለው በብርሃኑ እና ንአምን በቀላሉ ሊሸወድ እንደሚችሉ ጥርጥር የለኝም።

አንባቢዎቼ መረዳት ያለባችሁ፤ ግንቦት 7 ተጠግቶበት ያለው ድርጅት የአገራችን የተፈጥሮ ጠላት የሆነው ዓለም ያወገዘው ሻዕቢያ የተባለ አደገኛ የማፍያ ቡድን መሆኑን አትዘንጉ። ስለሆነወም፤ ግንቦት 7 "እንኳንስ ዘንቦብሽ እንደውም ጤዛ ነሽ" እንኳን እርዱን ብለው ተጠግተውት ገና ለገና እዚህ ውጭ እየኖሩም አመራሮቹ ስለ አገራችን ያላቸው የሉዓላዊነት አመለካካት ልክ እንደ ወያኔ ለሻዕቢያ ያላቸው ቅጥረኛነት በገልጽ ባደባባይ ነግረውናል። ስለሆነም፤ አመራሮቹ እሜዳው ላይ ሲገኙ የኢትዮጵያ አርበኞች ግምባር የሚባለው በጉልበት ታጥሮ የተያዘ ጥቂት ሰራዊት ስለ የኢትዮጵያ እና ኤርትራ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ምንና እንዴት ዓይነት ትምህርትና ቅስቀሳ ማስተማር እንዳለባቸው፤ የት እና እንዴት መሰልጠን ወይንም የትና የት ኤርትራ ድምብር ውስጥ መንቀሳቀስና ጦርነት ዘመቻ ማከናወን እንዳለባቸው....ወዘተ..ወዘተ.. ወዘተ... ሻዕቢያ መሪዎች በሜመራንደም/ ውል ያስገቧቸዋል። ይህም በፊርማ የሚረጋገጥ ነው።

አንዴ አስመራ ሄደው ታጋዮችቻውን መስረተዋል እና ሻዕቢያ ከሚሰጣቸው መመሪያ ፈቀቅ ብለው "እምቢ" ብለው ማንገራገር እንኳ ቢፈልጉ፤ እነሱንም ሆነ ሠራዊታቸው አደጋ ላይ እንደሚወድቁ ስለሚያውቁ፤ "ምርጫቸው፤ የታዘዙትን" መፈጸም ግዴታቸው ነው። እንኳን እዛው ሄደው፤ እዚህም የግንቦት 7 መሪዎች በስራ አስኪያጅነት በሚመሩት የኢሳት የዜና ጣቢያ እንኳ ስለ ሻዕቢያ እና ስለመሪያቸው ምንንት ወይንም ስለ የኤርትራ ሕዝብ አሰቃቃ ህይወት መናገር ከቶ አይፈቀድላቸውም።

የወያኔ ታጋዮች ወደ ኤርትራ ለስልጣና በሄዱበት ወቅት የደረሰባቸው ንቀት ጉድ አስገደ በትግርኛ መጽሐፉ ጠቅሶታል። ኢሕአፓዎችም ስለ ኤርትራ ሉዓላዊነት እመኑ ተብለው "እናስብበታለን" ብለው ስላንገራገሩ የኋላ ኋለ ሻዕቢያ በወያኔ እንዴት እንደተካቸው የምታውቁት ታሪክ ያለ ይመስለኛል። የእነዚህ ግን በጣም የባሰ ሊሆን ይችላል።ምክንያቱም የማታገያ ቦታ የለንም ብለው ስለተጠጉ። አረጣ ጠያቂ ደግሞ ጭንቅ ስለሆነበት 'አበዳሪው' የሰጠውን ስምምነት ፈርሞ ነው ብድሩን የሚያገኘው። ስለሆነም፤ ሉዓላዊነታችንን "ለገበያ/ኮምፐሮማይዝ" የማድረጋቸው ቅሌት በተጠናከረ ሂደት "ቅጥረኞች" ሆነው ዳግማዊ ወያኔ እንደሚሆኑ እኔ በበኩሌ አልጠራጠርም። የሚለፈልፉትን አንደበት ከትንፋሻቸው መረዳት አያዳግትም። "በጊዜ የጮኸ ጅብ ሲመሽ አያሳድረኝም" ይላሉ ትግሬዎች ወደ አማርኛ ስመልሰው።

የግንቦት 7 አመራሮች ስለ ኤርትራ ጥብቅናቸው ገና ሳይጅምሩ ያስተጋቡት ወያኔዎች <<መለስና ህወሓት ገና ክጅመሩ ወደ በረሃ ሲወጡ የተጨበጠ ፕሮግራም አልነበራቸውም። መፈክራቸው የደርግን አገዛዝ ጥለን ሕዝባዊ መንግሥት እንመሰርታለን ከሚል ውጪ ይህ ነው የሚባል ፕሮግራም አልነበራቸውም። ጎልታ ስትስተጋባ የነበረቺው መፈክራቸው 'ኤርትራ' ከኢትዮጵያ የተለየች ራሷን የቻለች አገር ናት፡ የምትለውን በቃል 'እንደ ዝናር ታጥቀዋት የመጡ ነበሩ" (ይላል፤- አስገደ ገ/ስላሴ የመለስ ራዕይ/ገ-55)፤ እነ ግንቦት 7 አመራሮችም ኤርትራ ራሷን የቻለች አገር ነች፤ ግንቦት 7 ይህንን ሕጋዊ ሉዓላዊነታችሁ ዓሰብን ጨምሮ እናከብራለን። ይህንን ነጻነታችሁ እና ሉዓላዊ መሬታችሁን "እየተቀናቀኗችሁ" ያሉት ጥቂት "ነፍጠኞችን" በቁጥጥር ሥር አስገብተንላችኋል>> ብለው በግልጽ ለኤርተራኖች ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን ጀሮ እና ዓይን እየሰማን እና እያናቸው ካወጁ ፤ ወዳጅነታቸው እየተጠከረ ሲሄድ ከአመታት ቆይታቸው በኋላ ቅጥረኛነታቸውና 'የኮምቢሽታቶ ሽርሽር፤ የአስመራ መሎቲ' እየሞቃቸው "ባለ 5 ስታር ሆቴል እንክብካቤ እየተደረገላቸው እነ **"ሽኮሪና"** እና እነ **"ሰሚራ"** እጉያቸው ስር ታቅፈዋቸው እንዲያድሩ ሲፈቀድላቸው" የኋላ-ኋላ ምን ይዘውልን እንደሚመጡ መገመት አያዳግታችሁም።

**"ኣነ ጭራሮ እአሪ መድረሪና**
**ንሳ ተመን ትእክብ ቀታሊና"**

ይላሉ የጥንት ትግሬ ምሳሌ ነጋሪዎች፡(እኔ ለማገዶ 'ጭራሮ'/ቀጫጭን እንጨት እለቃቅማለሁ ፤ እሷ ደግሞ እባብ ትለቅማለች መግደያችን/ገዳያችን" ይላሉ።

ይህ የግንቦት 7 አመራሮች የተለያዩ ጸረ አንድነትና ሉዓላዊነት ንግግራቸው የሚያመላክት የቅጥረኛ ባሕሪ ንግግራቸውን ሕዝብ እንዲያውቀው ስንሞክር፤ የምንጽፈው ትችት

ወዳጆቻቸው የሆኑት የሚዲያ ባለቤቶች በሚዲያቸው አይለጥፉልንም። ምክንያቱም አስገደ ገ/ስላሴ ስለ መለስ እና ሙሰኞች ሲገልጽ እንዳለው፡-

“ …የሙሰኞች የማፊያ ቡድን ተቋቁሞ እነሱን ለማጋለጥ ያሰበ ዜጋ በእነዚህ ማፊያዎች ይገደላል። ማፊያዎቹ አስፈሪና የበላይነት ቦታ ይዘው የሚቀጥሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል” ( ገጽ 53) በተመሳሳይ መልኩ እኛም ስለ እነ ግንቦት 7 ቅጥረኛነት ስንተች ወይንም ስንጽፍ የማፊያ ምላስ የተቸሩ ተከታዮቻቸው በየፓልቶኩ ሲዝቱብን እና ሲዘልፉን ታደምጣላችሁ (መጽሀፍቶቼም እንዳይሸጡ የጣሩበት ወቅትም ነበር )። ይህ እናንተንም ጭምር የሚያስገርም በወዳጃቸውም ጭምር እየተፈጸመ ያለውን ክስተት አንድ ምሳሌ ልስጣችሁ፡-

**አበበ በለው** የተባለው የአዲስ ድምፅ ራዲዮ አዘጋጅ፤ የግንቦት 7 መሪዎችን በዛኛው ሰሞን የራዲዮ ንግግሩ “የዓይናችን ብሌኖች ናቸው” በማለት ከዓይኑ ብሌን ጋር እኩል የሚያወዳድራቸው ጸረ አማራ እና ጸረ ሉዓላዊነታችን የሆኑትን የግንቦት 7 አመራሮች፤ በቅርቡ የግንቦት 7 አመራራሮች ወደ ኤርትራ ከመጓዛቸው በፊት ይመስለኛል (ጁን 15/2015 የተጻፈ የራሱ ደብዳቤ እንደሚለው) ስለ ኢሳያስ አፈወርቂ ጉዳይና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን ይመስለኛል ‘ቅሬታውን’ በመግለጹ የተነሳ፤ የግንቦት 7 ጀሌዎች “በየፓልተኩ ክፍል” በዘለፋ እና በዛቻ አበበ በለውን “ሸንቅላጡ” ስላወጡት (ባማርኛ ምን እንደሚባል አላውቅም፤ በትግርኛ “ሸንቅላጡ አወጡት” ማለት “አፈር ድቤ (?) አበሉት” ማለት ይመስለኛል፤ ካልተሳሳትኩ። ሲዘልፉትና ሲያስፈራሩት ጊዜ፤ የሚከተለውን ደብዳቤ “ለዓይኖቹ ብሌን” ለነ ብርሃኑ እና አመራሮች ደብዳቤ እስከመጻፍ ተገድዶ መኖሩን ሳልገልጽላችሁ አላልፍም። ይህንን የሚከተለው የተማጽኖ ደብዳቤውን ስታነቡ እሚገርም የግንቦት7 ተከታዮች ባሕሪም ሆነ የደብዳቤ ጸሐፊው **“በምስጢር ያዙት”** የመማጸኑ ገትጎታ የሚያሳየን ነገር አለ። ሌላው የገረመኝ ዳኛ ብርቱካን መዲቅሳም የደብዳቤው ቅጅ ተደርጎላታል። ከትምህርት በኋላ ከነዚህ ቡድኖች እራስዋን አግልላ እየኖረች/እንደ ብርሃኑ ተራራ ላይ ወጥታ እየተመራመረች መስሎኝ ፤ ለካ በድብቅ ፖለቲካውንም አብራ እየተመራመረችብን ነው እባካችሁ፡ “ወይ ገረማርያም” ሞኙ! አለ የገረመው የትግሬ ገበሬ። ይህም አለ ለካ! እንዴት ከፖለቲካው ወደ ኋላ ቀርተናል እባካችሁ!? እነሆ አንብቡት-

June 15/2015
አዲስ ድምጽ
ለዶክተር ብርሃኑ ነጋ የአርበኞች ግንቦት 7 ሊቀመንበር፤ለአቶ ንአምን ዘለቀ ፤ የኢሳት ቴሌቪዥን ዋና ሥራ አስኪያጅ

ላለፉት ሃያ አራት አመታት የኢትዮጵያን ህዝብረግጦ እየገዛ ያለውን የህወሃት አገዛዝ ለማስወገድ በሚደረገው ትግል አዲስ ድምጽ ራዲዮ ያበረከተው አስተዋጽዖ ለእናንተ መናገሩአስፈላጊ አይሆንም። ይህ ራዲዮ ሁለታችሁም የምትመሯቸውን ድርጅቶች

መፈጠራቸውን ከማስተዋወቅ አልፎ ዛሬ ለደረሱበት ደረጃ ታላቅ አስተዋጽዖ ያበረከተ ግምባር ቀደም ጣቢያ መሆኑንየማትዘነጉት እናህዝብ የሚያውቀው ሀቅ ነው። ከሁሉም በላይ የመናገርመብታችው እንዲከበር፣ ያልወደዱትን የመቃወም የወደዱትም ደግሞ የመደገፍ ተፈጥሯዊ መብታቸው እንዲከበር ሁለታችሁም ህይወታችሁን የምትሰጡለት አላማችሁ መሆኑን በየተገኛችሁበት ህዝባዊ ስብሰባ ቃል የገባችሁለት ሃቅ ነው።

እነዚህ መብቶች እንዲከበሩ አዲስ ድምጽ ራዲዮ እና መስራቹ አበበ በለው ላበረከቱት አስተዋጽዖ ሁለታችሁም መስክራችኋል። በድርጅታችሁ ስምም ሽልማት አበርክታችሁልናል። ዛሬ የአርበኞች ግንቦት ሰባት አባላትም ህይወታቸውን ለመስጠት ተነስተዋል የተባለለት አላማም ኢትዮጵያዊያን የመናገር መብታችው እንዲከበር ነው። ይህ መብት ሳይሸራረፍ እንዲከበር እናንተም ሆናችሁ ኢሳት በየቀኑ ለህዝብ የምታስተምሩት ጉዳይነው።እነዚህን መብቶች ለማስከበር ባደረግነው ትግልም ግፈኛው የኢትዮጵያ አገዛዝ እኔ አበበ በለውን የግንቦት ሰባት ከፍተኛ አመራር ነህ፣ከኤርትራው ገዥ ኢሳያስ ጋር በመሆን ኢትኦጵያ በህዝብ የተመረጠን መንግስት በሃይል ለመጣል ይታገላል፡ በማለት ሁለታችሁ ያላችሁበት ከአስራ አምስት ጀግኖች ጋር በአንድመዝገብ ተከሠን፤ ዶክተር ብርሃኑ በሞት፣ እኔ በአስራ ሰባትዓመት፣ አቶ ነዓምንን በአስራ አራት ዓመት እንድንቀጣ መወሰኑም አይዘነጋም።

በቅርቡ ግንቦት ሰባት ከአርበኞች ግምባር ጋር በመሆን በኤርትራው ገዥ አቶ ኢሳያስ በሚደረግ እርዳታ በትጥቅ ህዋሓትን እንዋጋለን የሚለውን እንቅስቃሴ ለህዝብ ይፋ ሲያደርግ በተደጋጋሚ በኢሳት ቴሌቪዥን እና ራዲዮ ህዝብ እንዲደግፈው በተደጋጋሚ ሲገለጽ፤ እንዲሁም ለአለፉት አርባ አመታት ኢትዮጵያን ወግተዋል፤ ኢትዮጵያን ለመቶ ዓመት የሚያተራምስ የቤት ስራ ሰጥቻታለሁ በማለት የተናገሩት ኢሳያስ ምንም የሚጸጽታቸው ነገር በኢትዮጵያ ላይ እንዳልፈጸሙ በኢሳት መናገራቸው ይታወሳል።

ይህንን የሰሙ ኢትዮጵያዊያን ድጋፋቸውን እንጅ ተቃውሟቸውን በኢሳት ማስሰማት ሲከለከሉ፤ መስዋእትነት የከፈልንለትን የመናገር መብት በመጠቀም ተቃውሟችንን በአዲስ ድምጽ ራዲዮ እና በዳላስ ከተማ ሕዝባዊ ስብሰባ አድርገን ጥያቄ እንዳለን በይፋ በመግለጻችን፤ ድርጅታችሁን እንደግፋለን በሚሉ እና የድርጅታችሁ አባላት የየከተማው ተወከዮቻችሁ እያደረሱብን ያለው ከኢትዮጵያዊ ጨዋነት የማይጠበቅ ስድብ እና ስም ማጥፋት እየሰማችሁት እንደሆነ ጥርጥር የለኝም።

ይህ በጣም የሚያሳፍር ማስፈራራት እና ስም ማጥፋት ለምንታገለው አፋኝ ስርዓት በር ከመክፈቱም አልፎ የእነ እስክንድር ነጋን፣ርዕዮት አለሙን እና የሌሎችንም የመናገር መብታቸውን በመጠቀማቸው ብቻ  የታሰሩትን ወገኖቻችን ያለአግባብ መታሰራቸውን ዋጋውን  የሚቀንስ እና የእናንተ ድርጅት የሚያመጣው ነጻነት ሳይሆን ሌላ አፈና ነው ብለን እንድናምን የሚጋብዝ ሆኖ ተሰምቶኛል። ልክ አይደለም ቀይሩት ያልነውን አፈና እኛ ስናደርገው “ልክ ከመሰለን” በአፋኞች የታፈነውን ነጻ ልናወጣው **ሳይሆን** በተራችን ልናፍነው እንደሆነ እየነገርነው ነው።

ስለሆነም ይህን በተቃዋሚው መሃል የማይበርድ ልዩነት **ሊያስነሳ** የሚችል ስርዓት የጎደለው የአባሎቻችሁና የደጋፊዎቻችሁ ስም ማጥፋት እና ስድብ በሰለጠነ ውይይት፣ ከተቻለም በክርክር የመግለጽ መብት እንዲያከብሩ በግልጽ እንድትተባበሩኝ ለዚህ ችግር መፍትሄ ለመስጠት በኢሳት እና በአዲስ ድምፅ ቀርባችሁ ትብብራችሁን እንድታሳዩኝ በምትታገሉለት እና የነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞች በታሰሩበት ዓለማ ስም እጠይቃልሁ።

ለዚህ ችግር መፍትሄ ለመስጠት በኢሳት እና በአዲ ስ ድምጽ በአጭር ጊዜ ቀርባችሁ ጉዳዩን መስመር እንድታስይዙት ፈጣን ትብብራችሁን አንድታሳዩኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ።
ማሳሰብያ፤- ይህ መልእክት ለመገናኛ ብዙሃን እንዳይውል አዲስ ድምጽ ራዲዮ በአክብሮት ይጠይቃል።

አበው ሲተርቱ ሳይቃጠል በቅጠል ይላሉ እና እኛም ተያይዘን ሳንነድ እሳቱን አብረን እናብርድ እላለሁ።

## “I do not agree with what you have to say, but I'll defend to the death your right to say it”. Voltaire

አበበ በለው
የአዲስ ድምጽ ራዲዮ መስራች፤ ከ፱ኙ የኢሳት መስራቾች አንዱ
ግልባጭ

- ለአዲስ ድምጽ ራዲዮ የድጋፍ ኮሚቴ
- ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ
- ለኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ
- ለኢትዮጵያ የሽግግር ምክር ቤት
- ለኢትዮጵያ ነጻ ጋዜጠኞች ማህበር
- ለፕሮፌሰር አለማየሁ ገ/ማሪያም
- ለዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ
- ለዳኛ ወልደሚካኤል መሸሻ
- ለዳኛ ፍሬህይውት ሳሙዔል
- ለጋዜጠኛ ሙሉጌታ ሉሌ
- ለጋዜጠኛ አብራሃ በላይ
- ለጋዜጠኛ ክንፉ አሰፋ
- ለጋዜጠኛ አበበ ገላው
- ለጋዜጠኛ አዲሱ አበበ
- ለጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና
- ለጋዜጠኛ ሰርካለም ፋሲል

□ ለጋዜጠኛ ሄኖክ አለማየሁ
□ ለጋዜጠኛ ሃብታሙ አሰፋ [Leaked Document reveals Ginbot 7 leadership rivals split ...](www.awrambatimes.com/?p=13665)
www.awrambatimes.com/?p=13665

ከላይ ያነባባችሁት ምናልባት ሊንኩን አንዳታጡት በሚል ከፒዲኤፍ ወደ ወርድ እንደገና በታይፕ ጽፌዋለሁ (እጅግ ያደከማል) ስሕተት ካለው የኔ መሆኑን ልገልጽ እወዳለሁ።

ይህ ሁሉ ጉድ እንግዲህ የግንቦት 7 መሪዎች በየቻፕተሩ/ቅርንጫፍ ያሉት ወኪሎቻቸው እና ተከታዮቻቸው የሚያሳዩት ዱርየነት ባሕሪ በወዳጃቸው በአበበ በለውም የተረጋገጠ ነው። እኛ ስንለው ግን የሚያምነን ሰው የለም። ምክንያቱም ጭፍን ሕብረተሰብ አድርገው የቀረጹት እነዚሁ ጋዜጠኞች ነን፤ የፖለቲካ መሪዎች ነን የሚሉ ናቸውና፤አንዴ ስለተሰለቡ እነሱ የሚሉት እንጂ እኛ የምንለውን ሃቅነት ቢኖሮውም አይቀበሉትም ።

ለዚህም እንደዚህ ያለ ቡድን ሥልጣን ላይ ከወጣ ከወያኔ እና ሻዕቢያ የባሱ ዱርየዎች አሰማርቶ ነብስ የሚገድሉና የሚገርፉ አንደሚሆኑ፤ ካሁኑ ምልክቱ ይኸውና "ከፈረሱ አንደበት" /ፍሮም ዘ ሆር'ስ ማውዝ/ ምስክርነት ሰጥቻለሁ።

የሚያሳዝነው ደግሞ ልክ አስቀድሜ ባለፈው ጽሑፌ እንደገለጽኩት፤ ሚዲያዎቹ ሁሉም ጋዜጠኞች በመሆናቸው እንደ እድር/ማሕበር የተደራጁ ስለሆኑ የጠበቀ ቡድናዊ/ (ሙያዊ ሳይሆን) ትስስር ስላላቸው፤ አንዱ የንግግር/የመጻፍ አፈና ሲያካሂድ፤ ለምን እንደዚህ ታደርጋለህ ብሎ የሚተቸው/የሚገስጸው ከውስጣቸው እምብዛም ስለሌለ፤ በኛ በጻሃፊዎች ላይ የፈለጉት አፈና ቢያደርጉብን ተሸፋፍነው አብረው ይጓዛሉ።

ለዚህም ምሳሌ ባለፈው ጽሒፌ የግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል የነበሩት "ግንቦት7 ዲሞክራሲ" በሚል ተነጥለው ከግንቦት7 ከብርሃኑ ነጋ ቡድን ከተለዩት ቡድኖች ጉዳይ ምሳሌ ሰጥቻችሁ ነበር። ብዙዎቹ፤ ኤርትራ እያሉ "አሰቃቂ ሰቆቃ" ድብደባ፤ርሸና፤የጉልበት የእርሻ ስራ፤ ርሃብ እንግልት፤ ወፌላላ (ሄልኮፕተር) የመሳሰሉ አንዳርጋቸው በወያኔ ከመያዙ በፊት እያለ በራሱ ትብብር ከኤርትራዎች ጋር ሆኖ ለዚህ ስቃይ እንደዳረጋቸው ሸሽተው እንደ ዕድል ከሞት ያመለጡ እያለቀሱ አንደነገሩን ገልጫለሁ። የኢሳት ጋዜጠኞችና ዋና አዘጋጆች (በወቅቱ ንአምን ዘለቀ ማለት ነው ፤ የግንቦቱ ዋናው ሰው! የጣቢያው ዋና ስራ አስኪያጅ ነበር! ይታያችሁ ፤ እንግዲህ! የልጆቹ እሮሮ ለምን አንደታፈነ ግልጽ ይሆንላችኋል) እና ቡዱኖቹ የነዚህ ልጆች እምባ እና አቤቱታ እንዳይደመጥ እንዳፈንዋቸውና፤ በሌሎች አገር ወዳድ ድረገጾችና ራዲዮኖች ትብብር አምባቸውንና እሮራቸውን እንድንሰማ መደረጉን ገልጫለሁ።

ሆኖም አበበ በለው ነፃ ንግግር እንፍቀድ ይበል እንጂ እሱም የዚህ ፈትል ቁራኛ እና አባል እንደመሆኑ መጠን ከላይ ደብዳቤውን ስታነቡ የሚለው "ማሳሰብያ፣ ይህ መልእክት ለመገናኛ ብዙሃን እንዳይውል አዲስ ድምጽ ራዲዮ በአክብሮት ይጠይቃል።" ሲል የግንቦት7 አባሎችና ጀሌዎች ዱርዬ ባሕሪያቸው በሕዝብ እንዳይታወቅ ተሸፋፍኖ እንዲቀር መጣሩ ነው። እንዲህ ዓይነት የአንድ የፖለቲካ ድርጅት አባሎች ባሕሪ ይፋ ሆኖ ሕዝቡ የድርጅቱ (ቻርተሮቹ ወኪሎች ሳይቀሩ በአበበ ደብዳቤ አቤቱታ መሰረት) ድርጅታዊ ጠንካራ ስነምግባር እንደሌላቸው  በሕዝቡ ሕሊና እንዳይገመገም፤ ሕዝቡ እንዳያውቃቸው፤ እንዲታፈን ሳያታወቀው/ወይንም በራሱ ያልገለጸልን ምክንያት ተባባሪ ሆኗል ማለት ነው።

ሕዝቡ የማወቅ መብቱም ቢሆን እነ ግንቦት 7 አባሎች ብዙዎቹ ዱርየነት ባሕሪ እንደሚያጠቃቸው በተሞክሮ የምናወቅ ጥቂቶች ብንሆንም፤ እኛ እንደምንከታተላቸው ብዙሃኑ ላይረዳቸው ስለሚችል፤ ታፍኖ የቆየን ዱርየ ባሕሪ እያደገ ሲሄድ፤ ጠመንጃ ሲታጠቅ፤ ወደ መንግስትነት ሲለወጥ ፡' "የጎስታፖ" ስራ ለመስራት የሚያግደው ስነ ምግባር አይኖርም ማለት ነው። ሕዝቡ ከእንደዚህ መሳይ ድርጅት መደገፍ መታቀብ አለበት።

ወያኔዎችም ሲያድጉ "ሕዝቡን፤ በማስፈራራት፤ዝም በማሰኘት፤ በመዝለፍ፤በመደብደብ፤ ስም በማጥፋት፤ንብረት በመቀማት፤ በመሰወር፤ ከሕብረተሰብ ማግለል፤ ወዘተ..ወዘተ..ወዘተ... ሲያደርጉ በማደጋቸው፤ ወደ መንግሥትነት ሲለወጡ አሁን የምናየው ጭራቅነት ባሕሪ ተላብሰው የምናያቸው፤ ከጅምሩ እንዲህ እያደረጉ በማደጋቸው፤ ሕዝቡን ዝም አሰኝተውታል።ስለሆነም.የአበበ በለው ስሞታ/እሮሮ ተገቢነት ቢኖሮውም "በምስጢር እንዲያዝ፤ሚዲያ እንዳያውቀው" ብሎ ሲል፤ "እከኩኝ፤ ልከክላችሁ" "የዓይኔ ብሌኖቼ ናችሁ እና አላጋልጣችሁም፤ እኛው በኛው" የማለቱን ባሕሪ አልወደድኩትም። ይህ ደግሞ ከጠበቀ ወዳጅነት፤ቁርኝት፤አብሮ መብላት መጠጣት፤እስከስታ መምታት፤ የሚንጸባረቅ ኮራፕት /የነቀዘ/ የሚዲያ ባሕሪ/አመል ነው።

አብሮ የመብላት፤ የመገናኘት ነውርነት ባይኖሮውም ከዚህ በታች የምታዩት ቪዲዮ (ብርሃኑ፤ ታማኝ፤ መሳይ፤ሲሳይ፤ንአምን፤  ወዘተ...ወዘተ...ማሕበራዊ ግንኙነታቸው ምንኛ የጠበቀ ፍቅር እንዳላቸው ስትምለከቱ "በፖለቲካ መደባበቁ" ላይ "እከከኝ ልከክህ"፤ ንቅዘትን የፖለቲካ መሸፋፈንን፤ ወንጀል የመደበቅ ባሕሪን ሊአስከትል ይችላል። እነኚህ ወደ መንግሥትነት ሲለወጡ፤የወያኔ ያህል ቡድናዊ "እከከኝ ልከክህ" ቤሰባዊነትና ጋብቻነት  ሊያድግ እንደሚችል በቀላሉ ከዚህ ክስተት መገመት ትችላላችሁ። ብርሃኑ ሲነካ እነ ሲሳይ አገና፤ ፋሲል፤ እነ ደረጀና መሳይ የመሳሰሉ የኢሳት ዋና ጋዜጠኞች እንዴት እንደሚቃጠሉ ስትመለከቱ 'አውነትም እነዚህ ሰዎች፤ የሕዝብ ጋዜጠኞች ወይስ የብርሃኑ/ የግንቦት 7 ጋዜጠኞች?" የሚል ብርቱ አግራሞት ያድርባችኋል። የሚዲያ ቁርቆዛ ከሥሩ እየተመገዘ እንዳለ ይኼውላችሁ፤ እከከኝ ለከክልህ ቪዲዮውን ከዚህ በታች ያለውን ተመልክቱልኝ።

አሊበደርቿ! በሚቀጥለው ሰሞን እንገናኝ፡ ከእግርጌ ያለው ቪዲዮ ማየቱን እንዳትረሱ እነሆ ተመልከቱት፤- ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያነ ሰማይ አዘጋጅ) getachre@aol.com Ethiopian Semay

**Will it be so easy for Berhanu Nega to abandon this comfy life**

https://youtu.be/lb1ULKKb9aU